መመሪያቁጥር 05../2010

# በልውጥ ሕያዋን ላይ ለሚደረግ የጠንቅ ግምገማ የሚያገለግሉ መስፈርቶችን ለመወሰን የወጣ መመሪያ

በልውጥ ሕያዋን ላይ የሚደረግ ማንኛውም እንቅስቃሴ በተገቢው የጠንቅ ግምገማ ሂደት ማለፍ ያለበት በመሆኑ፤

የልውጠ ሕያዋን የጠንቅ ግምገማ ለማድረግ ቁልፍ መስፈርቶችን መለየት አስፈላጊ በመሆኑ፤

የአካባቢ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር ስለደሕንነተ ሕይወት ባወጣው አዋጅ ቁጥር 655/2001 (በአዋጅ ቁጥር 896/2007 እንደተሻሻለው) አንቀጽ 25 መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል::

## ክፍልአንድ
## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ "በልውጥ ሕያዋን ላይ ለሚደረግ የጠንቅ ግምገማ የሚያገለግሉ ቁልፍ መስፈርቶችን መወሰኛ መመሪያ ቁጥር 05/2010" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

2. **የተፈፃሚነት ወሰን**

   ይህ መመሪያ ከግንዛቤ የመነጨ ስምምነት ወይም ልዩ ፈቃድ ገና ሳይሰጣቸው በልውጥ ሕያዋን ላይ ማንኛውም ዓይነት እንቅስቃሴ ለማካሄድ በሚቀርብ ጥያቄ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል::

3. **አጠቃላይ መረጃዎች**

   የልውጥ ሕያዋን የጠንቅ ግምገማ መስፈርቶች፣

   1/ በልውጥ ሕያዋን ማንኛውንም ዓይነት እንቅስቃሴ ላይ የሚሰማራ ሰው በሰው ወይም በእንስሳት ጤንነት እንዲሁም በአካባቢ ሊኖር የሚችለውን ጉዳት ለመለየት አስቀድሞ የጠንቅ ግምገማ ማካሄድ አለበት፤

   2/ ለተጤነ ልቀትና ለዝግ አጠቃቀም እንቅስቃሴዎች የሚያስፈልገው የመረጃ መጠን ሊለያይ ይችላል፤

   3/ በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ሚኒስቴሩ የማህበራዊ እና ኢኮኖሚዊ ሁኔታዎችን ከግምት ሊያስገባ ይችላል::